ፓለቲከ፣ ዘር፣ ሐይማኖት የማይለይ የአንድነት ፀሎት ጥሪ ለቴወድሮስ ካሳሁን  (ቴዲ አፍሮ)

# “በአንድነት ከገባን የፍቅር ሱባኤ”

ይኸን የወንድማችንን ቴወድሮስ ካሳሁን አባባል መሰረት በማድረግ አብሮ አደግ ጋደኞቹ (“የቤተልሔ ም ትምህርት ቤት ተማሪወች”) በየእምነታችን በፆምና በፀሎት ልናስበው አቅደናል: ለዚህም ቅዱስ እቅድ  ለመሳተፍ የምትፈልጉ የቴወድሮስ ካሳሁን አድናቂወች፣ ዘመድ ወዳጆች  በያላችሁበት በመሆን ፓለቲከ፣ ዘር ፣ሐይማኖት ወደማይለየው ወደፈጣሪያችን እግዚያብሔር እንድትማፀኑ  በትህትና እንጠይቃለን::

## “ፍቅር አጥተን እንጂ”

ፍቅር ያስታግሳል ፣ፍቅር ያስተዛዝናል

ፍቅር አያቀናናም ፣ፍቅር አያስመካም

ፍቅር ልቦናን አያስተብይም፣ ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም

ፍቅር አያበሳጭም ክፍ ነገርን አያሳስብም

ፍቅር ለዘወትር አይጥልም

## የፀሎቱ አላማ

“በአንድነት ከገባን የፍቅር ሱባኤ” የሚለው የወንድማችን ሕልም አስተሳሰቡ ምኞቱ በእውን ተፈጽሞ እንዲያይና ሁሉን የሚፈጽም እግዚያብሔር አምላክ ፀሎታችንን ኢንድቀበል የፍቅር አምላክ እንዲጉበኘን እንማልዳለን:

ለወንድማችን ቴወድሮስ ይኸን እንዲያደርግለት እንለምናለን በጭንተቀቱ ጊዜ መረጋጋትን፣ በሐዘኑ ጊዜ መጽናናትን ፣ በተከዘ ጊዜ ተስፋን ፣በፀለየ ጊዜ መልሱን እንዲያገኝ በፆም በፀሎት እናስበው:

## ፀሎቱ

ሰውን የምትወድ መሐሪና በደልን ሁሉ ይቅር ባይ የሆንክ እግዜያብሔር አምላክ ሆይ እጅግ ተ ቸግረናለና ታውከናልና ምህረትህ ፈጥኖ ይደረግልን የቀድሞውን በደላችንን ሁሉ አታስብብን ስለቅዱስ ስምህ ስትል ሀጥያታችንን ሁሉ ይቅር በለን

ቸር እረኛ ሆነህ የምትመራን የምትጠብቀንና የምትመግበን አምላካችን እግዚያብሔር ሆይ ይህ የምንኖርበት ሥጋዊ አለም በረሀብ በጥማት በማለያየት በቂም በቀል ተሞልቷል ስለዚህም ከሰላም ማጣትና ከፍቅር አንድነት መቀዝቀዝ የተነሳ አንደጠፉት በጐች ሆነን እንዳንቀር ትሰበስበን ዘንድ እንማልድሀለን:

ሀገረ እግዚያብሔር ኢትዮጵያን እጆችዋን ወደ አንተ በፀሎት በምትዘረጋበት ጊዜ በአይነ ምህረት ተ መልከታት ለቅድስ ስምህ ክብር ስለምህረትህ እልል እያልን የምናመሰግንበትን ዘመን ምሕረትን አምጣልን ከቁጣህን በትዕግስት መልሰን በአየነ ምህረት ተመልከተን ፀሎታችንን ተቀበልልን ፀጋህንም አብዛልን:

ለዘለአለሙ አሜን